በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ




# ከጁላይ 1-10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

# ከጁላይ 11-20 እና ከጁላይ 21-31/2026 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2026


አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ሀዋሳ 35.6፣ ባህርዳር 23.3፣ ቢሾፍቱ 23.5፣ 33.1፣ 32.1፣ ጎንደር 40.1፣ 26.1፣ 23.5፣ ጎሬ 21.2፣ 23.5፣ ጅማ 28.7፣ ነቀምት 38፣ 61፣ 23፣ 28.3፣ 38.6፣ አይራ 28.2፣ አማን 26.2፣ 27.6፣ 51.9፣ አምቦ 29፣ አይከል 21.6፣ 27፣ በደሌ 21፣ 52፣ 21.4፣ 21.3፣ ቦሬ 26.6፣ ቡለን 20.4፣ 61፣ 35.4፣ ቡሬ 45፣ 27፣ ቻግኒ 24.2፣ 42፣ 49.2፣ ጭራ 23.6፣ ደባርቅ 26፣ ደብር ታቦር 48፣ ደምቢዶሎ 30.5፣ 20.2፣ 31.5፣ 20.1፣ ጋምቤላ 27.3፣ 65.6፣ ጋቲራ 21.3፣ 28.3፣ ገለምሶ 27.4፣ ጊምቢ 25.3፣ 43.1፣ እምድብር 22.2፣ ሊሙገነት 44፣ አዳማ 30.9፣ ሻሁራ 33.8፣ ሻምቡ 34.2፣ ሽሬ 21.9፣ 28.1፣ ወላታ ሶዶ 23.4፣ ባቱ 35.5፣ አቦ ሞሪንጋ 25.5፣ አዲስ ዘመን 21፣ 38.6፣ 39.9፣ አጋሮ 20.5፣ 32.2፣ 28.3፣ 23.5፣ አንጋጫ 22፣ አሺ 28፣ 20.4፣ 22.4፣ አሸሬ 37.8. አታንጋ 46.2፣ መንደር7 20.3፣ ደነባ 50.2፣ እንዳባጉና 30.6፣ 38፣ 22.9፣ ጋሳይ 21.2፣ ጋሸና 22.6፣ ሃሮ 31፣ 20.2፣ 20.1፣ ቅዳሜ ገበያ 27.8፣ 22.8፣ 26.6፣ 29.8፣ 21.7፣ 23.6፣ 38.9፣ 27.8፣ ኮበን 20.5፣ ማያንሳ 22.4፣ መከነኢየሱስ 21.4፣ 44.6፣ ኦንጋ 20.8፣ 33.4፣ ሺንዲ 46.5፣ ሲቦ 28.6፣ 21.8፣ ወርቃምባ 34.7፣ ባቡ 25.2፣ 21.3 እንዲሁም ገምቤ 22.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ31 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.1-65.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በሌላ በኩል  በቀን 8 በትግራይ ክልል  ክልተ አውላዕሎ  ወረዳ በተወሰኑ ቀበሎዎች በረዶ የቀላቀለ ዝናብ የዘነብ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ  የተወሰኑ የእርሻ ቦታዎች በደለል ተጥለቅልቀዋል፡፡ በተጨማሪም በመካነኢየሱስ ከተማ ከነበረዉ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ጎርፍ ተከስቷል፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ በህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ አዊ፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ ፣የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ31-260 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ጁላይ 1 እስከ 10 /2026
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ጁላይ 1 እስከ 10 /2026
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ በህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ አዊ፣ከትግራይ ክልል የምዕራብ ፣የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞኖች፣ አዲስ አበባ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ጁላይ 1 እስከ 10 /2026
የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት ቀናት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ነበራቸው። ይህም የተገኘዉ እርጥበት ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ያሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር የጎላ አስተዋፅዖ ነበረዉ። በተጨማሪም በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው እርጥበት የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበቱም በላይ የተሻለ የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲኖር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንድሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች መጠነኛ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት የነበረ ሲሆን በተጨማሪም የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ መጠነኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው(ካርታ 4) ።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ በላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት ላይኛው ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። በተጨማሪም ተከዜ፣ አባይ፣ በላይኛው አዋሽ፣ በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሚደርስ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው። ይህ ሁኔታ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የውሃ መጠንን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን በተጨማሪም የመስኖና የሃይል ማመንጫ እንዲሁም የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅዎ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 5)።





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በጁላይ ሁለተኛ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው እና ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 5)። በመሆኑም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5 እና 6)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20 /2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.1 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20 /2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጥቂት የምስራቅ ቦረና ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| | አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ምስራቅ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የፋንቲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣ ዳዋ እና ሊበን ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ


በጁላይ የሁለተኛው አስር ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊ ዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ29 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 ኢ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20 /2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.3 ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የጁላይ ሦስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እሰከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እሰከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-29 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 9)፡፡




ካርታ 9 ኢ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31 /2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት የሚኖራቸዉ ሲሆን በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀምና የሚጠበቁ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2) ፡፡

## 2.5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት በጁላይ የሁለተኛ አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው የገጸምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3) ፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ አዊ ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ፣ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፤አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | ➢ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መሻሻል<br>➢ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገትና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት | ➢ የእርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቅየት እና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>➢ ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ<br>➢ የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት<br>➢ የአረም መከሰት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት<br>➢ የናዳ ስጋት ሊያመጣ ይችላል | ➢ የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር ሰብሎችን ዘር መዝራት<br>➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘሩ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ የመሬት መንሸራተት ተጋላጭነትን መቀነስ<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>➢ አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር<br>➢ የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በየጣልቃው የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶችን በመጠቀም መሰብሰብ |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጥቂት የምስራቅ ቦረና ዞን ፤ ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ምስራቅ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤የፋንቲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ፣ ሲቲ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣ ዳዋ እና ሊበን ዞኖች | ➢ ለመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት ምቹነት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ ለከተማ አካባቢ ግብርና ስራ | ➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤<br>➢ የአፈርና ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን<br>➢ የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በቂ መሆኑን በማረጋገጥ የመኸር ሰብሎችን ጊዜውን ጠብቆ መዝራት<br>➢ የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ ለደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ የአፈር እቀባ ስራ ማከናወን፤<br>➢ የእንስሳት ግጦሽ ሣር በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤<br>➢ የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በየጣልቃው የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም መሰብሰብ<br>➢ የናዳና የመሬት መንሸራተት ስጋት ተጋላጭነትን መቀነስ |

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከባድ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ ላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ እንዲሁም አዋሽ | • የዉሃማ አካለት የውሃ መጠን መጨመር<br>• ግድቦች የውሃ ይዘት መጨመር<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>• የሃይል አቅርቦት መሻሻል<br>• የከርሰ ምደር የውሃ መጠን መጨመር | • የቅጽበታዊ ጎርፍ ስጋት ሊኖር ይችላል<br>• የወንዝ በደራሽ ውሃ ሙላት<br>• የደለል ሰጋት መጨመር | • የተቀኛጀ የጎርፍ ቅድመ መከላከል ስራዎች መስራት<br>• የውሃ መውረጃ ቱቦዎች ማጽዳት<br>• በጥንቃቄ ማሽከርከር፣ ወራጅ ውሃን በእግርም ሆነ በተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር አለመሞከር |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| በላይኛውና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ መካከለኛውና ታችኛው ተከዜ፣ እንዲሁም በጥቂት ላይኛው አፋር ደናክል፣ | • መጠነኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በመጠኑ መሻሻል | • አንጻራዊ የትነት መጨመር<br>• የደረቅ ሰሞናት በመብዛት | • የሚገኘውን መጠነኛ ዉሃ በአግባቡ መያዝ<br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በመጠቀም የጊዜ ተመን እቅድ ማዘጋጀት |
| **በደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ መካከለኛና ታችኛው አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ | • የጎርፍና የደለል ስጋት መቀነስ<br>• በደራሽ ቆሻሻ ብክለት አለመኖር | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • ዉሃን በአግባቡ መጠቀም<br>• የውሃ ማሰባሰብና ማከማቻ ማጠናከር |